# የቅናሽ ክፍያ፡ እኛ ለመርዳት በእዚህ እንገኛለን!

ፓርኮችና የመዝናኛ ክፍሎች፣ ካምፖች፣ የአካል ብቃት አባልነት፣ የቅድመ ትምህርት ቤት፣ ፕሮግራሞችና ሌሎችም እርስዎ መክፈል የሚችሏቸው ዋጋዎች ናቸው! የእኛ የቅናሽ ክፍያ ፕሮግራማችን ለሁሉም ሰው፣ በሁሉም ቦታ፣ በየቀኑ የሚያግዝ ነው! ለሁሉም ተደራሽ ነው። ይህ ለአጭር ወይም ለረጅም ጊዜም የሚሆንዎ ነው።

ቅናሾች በጠቅላላ የቤተሰብ ገቢና መጠን ላይ መሰረት ያደረጉ ሲሆን ይህም በአሁኑ ጊዜ ከታተመው የ HUD ክፍል 8 የገቢ ገደቦች አንጻር የሚታይ ነው።

| **ክፍል 8 የ % አማካይ ገቢ ትርጓሜዎች** | | | | | **የገቢ ገደቦች ከሜይ 2026 ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናሉ** | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| % የቤት ክፍያ | የቤት መጠን | | | | | | | |
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 or More |
| 25% ክፍያ | **$34,900** | **$39,900** | **$44,900** | **$49,850** | **$53,850** | **$57,850** | **$61,850** | **$65,850** |
| 50% ክፍያ | **$58,150** | **$66,450** | **$74,750** | **$83,050** | **$89,700** | **$96,350** | **$103,000** | **$109,650** |
| 75% ክፍያ | **$74,800** | **$85,450** | **$96,150** | **$106,800** | **$115,350** | **$123,900** | **$132,450** | **$141,000** |

የቤተሰብዎ ገቢ ከመነሻው ገደብ በታች ሆኖ ከተገኘ አብዛኛዎቹ ክፍያዎች ሊቀነሱ ይችላሉ። ማንኛውም የቤተሰብ አባል ለቅናሽ ክፍያ ብቁ የሆነ ክፍያ ቅናሽ ማግኘት ይችላል።

ይህን ያውቃሉ? በእርስዎ ቤተሰብ ውስጥ ያለ አንድ ሰው ለነጻ ወይም ለቅናሽ ምሳ ወይም ከአርሊንግተን ካውንቲ የሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ ስር ለአገልግሎት ብቁ ከሆነ ከ 25% እስከ 75% ለሚደርስ ቅናሽ ክፍያ ብቁ ይሆናል።

ሁሉም የአርሊንግተን ካውንቲ ፓርኮችና መዝናኛ ፕሮግራሞች፣ ክፍያዎችና አገልግሎቶች ከግል ስልጠና፣ ለአዋቂዎች የግል መዋኛ፣ ለአዋቂዎች ሊግ፣ ለሚኖሩ ዝግጅቶች ክፍያ ወይም ለኪራይ ካልሆነ በስተቀር ለቅናሽ ክፍያ ብቁ ናቸው። አንዴ የቅናሽ ክፍያው በቤተሰብ ሒሳብ ላይ ከተተገበረ ቅናሹ መክፈያ ላይ በራስሰር ይተገበራል።

# ማመልከት የምችለው እንዴት ነው?

1. የማንነት ማረጋገጫ
2. የመኖሪያ ፈቃድ ማረጋገጫ
3. የገንዘብ ፍላጎት ማረጋገጫ

**የእያንዳንዱ አይነት ዝርዝር በዚህ ገጽ ጀርባ ላይ ተካቷል።**

arlingtonva.us በመጎብኘት 'የቅናሽ ክፍያ' በመፈለግ የመስመር/ኦንላይን ላይ የማመልከቻ ቅጽ ይሙሉ፣ ወይም

ሰነዶችዎን ከታች ከተዘረዘሩት ቦታዎች ወደ አንዱ ይዘው ይምጡ።

## የአካባቢ ዝርዝሮችና ሰአቶች

**Arlington Mill Community Center**
909 S Dinwiddie St., 22204
Sun. 1-7pm, M-F 7am-9pm, Sat. 8am-5pm

**Barcroft Community Center**
4200 S Four Mile Run Dr., 22206
Sun.1-7pm, M-F 8am-9pm, Sat. 8am-5pm

**Fairlington Community Center**
3308 S Stafford St., 22206
M-F 8am-9pm, Sat. 8am-5pm

**Gunston Community Center**
2700 S. Lang St., 22206
M-F 6-9pm, Sat. 9am-5pm

**Langston-Brown Community Center**
2121 N Culpeper St., 22207
M-F 9am-9pm, Sat. 9am-5pm

**Lubber Run Community Center**
300 N Park Dr., 22203
Sun. 1-7pm, M-F 7am-9pm, Sat. 8am-5pm

**Thomas Jefferson Community Center**
3501 S 2nd St., 22204
M-F 7am-9pm, Sat. 8am-5pm

**Walter Reed Community Center**
2909 16th St S, 22204
Sun. 1-7pm, M-F 8am-9pm, Sat. 8am-5pm

## 1 የማንነት ማረጋገጫ

በቤተሰብ ውስጥ ለሚኖር ለእያንዳንዱ አዋቂ (18+) ከመንግስት ኤጀንሲ የተገኘ አንድ ሰነድ (ምሳሌዎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ)

- በ DMV ወይም በሌላ ኤጀንሲ የተሰጠ ትክክለኛ የአሜሪካ መንጃ ፍቃድ ወይም የ VA ስቴት መታወቂያ
- ፎቶ ያለው የዩኤስ ፓስፖርት
- ፎቶ ያለው ቋሚ የመኖሪያ ካርድ (ወይም የነዋሪነት የውጭ ዜጋ ካርድ)

## 2 የመኖሪያ ፈቃድ ማረጋገጫ

ከሚከተሉት ሰነዶች ውስጥ አንዱ:

- በ DMV ወይም በሌላ ኤጀንሲ የተሰጠ ትክክለኛ የአሜሪካ መንጃ ፍቃድ ወይም የ VA ስቴት መታወቂያ
- በአርሊንግተን ውስጥ ለንብረት የሚሆን ኦርጅናል የሊዝ ውል
- ስም ያለበት የአርሊንግተን የግል ንብረት የግብር ሂሳብ ይህም ቀኑ ከ 12 ወራት ያልበለጠ
- ስም ያለበት የአርሊንግተን ሪል እስቴት የግብር ሂሳብ ይህም ቀኑ ከ 12 ወራት ያልበለጠ
- ስም ያለበት የአርሊንግተን የፍሳሽ/የውሃ ሂሳብ በስም ይህም ቀኑ ከ 12 ወራት ያልበለጠ
- ስምና የአርሊንግተን ካውንቲ አድራሻ ያለበት ትክክለኛ የመኪና ምዝገባ
- የንብረት ማስያዣ/የስመርስት ሰነድ
- የአርሊንግተን ካውንቲ የንብረት ግብር መግለጫ

## 3 የገንዘብ ፍላጎት ማረጋገጫ

የአርሊንግተን ካውንቲ የሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ ደንበኞቻቸው ለፓርኮችና መዝናኛ መምሪያ ብቁ መሆናቸውን ሁኔታቸውን እንዲያሳውቅ ጉዳያቸውን የያዘውን ሰራተኛ መጠየቅ ይችላሉ።

የሚከተሉት ሰነዶች በሰነዱ ላይ ለተዘረዘሩት ግለሰቦች ብቻ ብቁ ይሆናሉ፡-

- ልጅና ቤተሰብ ወይም IDD አገልግሎቶች ውስጥ የ DHS ሰራተኛ የብቃት ማረጋገጫ ደብዳቤ
- ባለፉት 12 ወራት ውስጥ የተመዘገቡ የግብር ተመላሾች (1040 ወይም 760)
- የሜዲኬድ ካርዶች ወይም ደብዳቤ ከቤተሰብ አባላት ጋር
- ለስራ አጥነት ማረጋገጫ የሚሆን ከመንግስት ኤጀንሲ የተላከ ደብዳቤ፣ “የአዋቂዎች የግለሰብ ምዝገባ ብቻ።”
- ለነጻ ወይም ለቅናሽ ምሳ ብቁ መሆንን የሚያረጋግጥ አሁን ላይ የተሰጠ የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት
- ጊዜያዊ እርዳታ ለተቸገሩ ቤተሰቦች (TANF) ወይም የምግብ ራሽን
- የሴት፣ ጨቅላና የሕጻናት ሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ ፕሮግራም (WIC)
- የምግብ ራሽን፣ ተጨማሪ የምግብ እርዳታ ፕሮግራም (SNAP)

ለአንድ ግለሰብ ገቢን ማረጋገጥ የሚችሉ ሰነዶች። ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ከቀረበ፣ ግለሰቡ ብቻ (የቤተሰብ አባላት ያልሆኑ) ለቅናሽ ክፍያ ብቁ ይሆናል፡

- ቤት ደብዳቤተጨማሪ የደህንነት ገቢ (SSI)
- የማህበራዊ ዋስትና የአካል ጉዳት መድን (SSDI)
- ስራ አጥ አዋቂ ግለሰብ (ሌላ ማንኛውም ገቢ ከክፍል 8 መመሪያዎች በላይ እስካልሆነ ድረስ)። ለማረጋገጫ ተቀባይነት ያለው ትክክለኛ የስራ አጥነት ቼክ ወይም መግለጫ ወይም ከቀድሞው አሰሪ የተላከ ደብዳቤ ማሳየት ያስፈልጋል።

እባክዎን ያስታውሱ፡ ሰራተኞቹ ለጥያቄው ድጋፍ እንዲሆን የሰነድ ቅጂዎችን ያስቀራሉ።

## ማመልከቻዎን ዛሬ ያጠናቅቁ

በአሁኑ ጊዜ በሚከተሉት የአርሊንግተን የሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ (DHS) ወይም የማህበረሰብ ፕሮግራም(ሞች) ውስጥ ከተመዘገቡ ምንም ተጨማሪ ሰነዶችን ሳያቀርቡ ዛሬ በመስመር/ኦንላይን ላይ ማመልከት ይችላሉ፡

- የ DHS ጥቅማ ጥቅሞች ወይም ድጎማዎች (ለምሳሌ፣ የመኖሪያ ቤት ድጎማዎች፣ ሜዲኬድ፣ TANF፣ SNAP፣ የልጅ እንክብካቤ ድጎማ፣ የአደጋ ጊዜ እርዳታ)
- የ DHS የአእምሮ/የአካላዊ ጤና አገልግሎቶች (ለምሳሌ፡ የህዝብ ጤና ክሊኒኮች፡ የጥርስ ህክምና ክሊኒኮች፡ የባህርይ ጤና፡ የአደንዛዥ እጽ አጠቃቀም፡ የእድገት እክል አገልግሎቶች
- ሌሎች የ DHS አገልግሎቶች (ለምሳሌ፣ ከፍተኛ የትራንስፖርት/የአመጋገብ አገልግሎቶች፣ ቤት የሌላቸው አገልግሎቶች፣ የነርሲንግ ጉዳይ አስተዳደር)
- የ DHS ቤተሰብ ድጋፎች (ለምሳሌ፡ WIC፣ የማደጎ እንክብካቤ)

### የገንዘብ ችግር

ቤተሰብዎ የገንዘብ ችግር ያለበት ሆኖ ከሆነ ነገር ግን የቅናሽ ክፍያ የብቃት መስፈርቶችን የማያሟላ ሆኖ ከተገኘ ለተወሰኑ ክፍያዎች እስከ ስድስት ወር ያህል ጊዜ ከችግር ነጻ ለመሆን ማመልከት የሚችሉበት በተለየ ሁኔታ የሚታይ ሂደት አለ። ለጊዜያዊ የገንዘብ ችግር ጥያቄዎች የገንዘብ ችግር መጠየቂያ ቅጽን በመሙላት በጽሁፍ መቅረብ ይኖርበታል። የተገለጸው ክፍያ ለመክፈል አለመቻልን መነሻ በማድረግ ችግሩ እንዲጸድቅ ይወሰናል።

የገንዘብ ችግር መጠየቂያ ቅጽ ቀደም ሲል በተዘረዘሩት የማህበረሰብ ማእከላት ውስጥ በመስመር/ኦንላይን ላይ ወይም በአካል በመቅረብ ሊገኝ ይችላል። አንዴ ከተጠናቀቀ፣ እባክዎ የተሞላውን ማመልከቻ ከሰነድ ጋር በማድረግ በ AccessDPR@arlingtonva.us ይላኩ

**ሁሉም ሰው • በሁሉም ቦታ • በየቀኑ**